የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ
ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ
ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ
ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ
ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3፥16-17



«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)፥130


**Global Good News Literature**
**የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት**
**P.O.BOX 451336**
**Los Angeles, CA 90045**
email: info@globalgoodnews.org


**Copyright © 2008**




## ማውጫ

ክፍል ፪


| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት ስድስት፡- መንፈሳዊ ውጊያና የአማኝ ሥልጣን ............... | 5 |
| መንፈሳዊ ውጊያ ስንል ምን ማለታችን ነው? ............................... | 5 |
| ፩. ውጊያ ካለ ጠላት አለ ................................................... | 5 |
| ፪. የሰይጣን የውጊያ መንገዶች ............................................ | 6 |
| ፫. በአንጻሩ ወንጌል እንዲህ ይላል፡-...................................... | 9 |
| ፬ ለአማኝ የተሰጠው መፍትሔ ምንድን ነው? ....................... | 9 |
| ፭. የአማኝ ሥልጣን ......................................................... | 10 |
| ትምህርት ስድስት፡- መንፈሳዊ ውጊያና የአማኝ ሥልጣን - ጥያቄዎች | 14 |

## <u>የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት</u>
## <u>የመላላክ ትምህርት</u>

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው። «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው። ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን።

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል። ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል። ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ።

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል። አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው። ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን።

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን።





# ክፍል ፩



**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤**
**ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»**
**መዝ. 118(119)፥130**

## ትምህርት ስድስት:- መንፈሳዊ ውጊያና የአማኝ ሥልጣን

### መንፈሳዊ ውጊያ ስንል ምን ማለታችን ነው?

መንፈሳዊ የሚለው ቃል፣ በዐይን ከምናየው ዓለም ውጭ የሆነውን የማይታየውን ዓለም ሲያሳየን፣ ውጊያ የሚለው ቃል ደግሞ በሁለት ተቃራኒ ኀይሎች መካከል ያለውን ጦርነት ያመለክታል::

መንፈሳዊ ውጊያ ስንል፣ በአማኝና በሰይጣን መካከል የሚካሄደውን መንፈሳዊ ጦርነት ማለታችን ነው:: ስለ መንፈሳዊ ጦርነት ስናስብ፣ እግዚአብሔርንና ሰይጣንን በማስተካከል ሰይጣን እግዚአብሔርን በቀጥታ መዋጋት ይችላል ማለታችን ሳይሆን፣ ሰይጣን የጽድቅ ጠላት ስለ ሆነ በምድር በጽድቅ የሚመላለሱትንና በጽድቅ ለመመላለስ የሚሞክሩትን የሚቃወም የክፋት መንፈሳዊ ኀይል መሆኑን ለመጠቈም ነው::

ሰዎች ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ይዘው ወደ ጦርነት ሲሄዱ እነርሱ ጠላታቸውን፣ ጠላታቸውም እነርሱን ሊያጠቃና ሊያጠፋ ይፈልጋል:: በመንፈስም ዓለም «ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም» (ዮሐ. 10፥10) የሚመጣና የሚዋጋን ጠላት አለን::

### ፩. ውጊያ ካለ ጠላት አለ

**ጠላት ማነው?**

«ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና ...» (1ጴጥ. 5፥8)፤ «... መንግሥተ ሰማይ መልካም ዘርን የዘራን ሰው ትመስላለች፤ ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላት መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ:: ...» (ማቴ. 13፥24-25)፤ «...እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፤ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው ...» (ማቴ. 13፥39):: ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው ጠላታችን ዲያብሎስ (ሰይጣን) ነው::

### ሰይጣን እንዴት ጠላት ሆነ?

ሰይጣን መጀመሪያ የተፈጠረው ጠላት እንዲሆን አልነበረም:: ኀያሉን እግዚአብሔርን ሊያገለግሉ ከተፈጠሩት ከዋነኞቹና ከከበሩት መላእክት መካከል አንዱ ነበር::

የእግዚአብሔር ቃል ስለ እርሱ እንዲህ ይላል:-

- ጥበብን የተሞላህ፣ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ::
- የከበረ ዕንቍ ሁሉ ... ልብስህ ነበረ፤
- በእግዚአብሔር ገነት በዔደን ነበርህ፤
- አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፤





- በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ
- በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ::
- ከተፈጠርህበት ቀን ጀምሮ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ (ሕዝ. 28፥12-15)::

ነገር ግን ከክብሩ ብዛት የተነሣ ልቡ እንደ ኰራና በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፀ፣ በዚህም ምክንያት ከነሠራዊቱ ከሰማይ እንደ ተጣለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: «አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? ... አንተም በልብህ ወደ ሰማይ አርጋለሁ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፤ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ ከደመናዎችም ከፍታ በላይ አርጋለሁ፤ በልዑልም እመስሳለሁ አልህ፤ ነገር ግን ወደ ሲኦል፣ ወደ ጒድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ::» (ኢሳ. 14፥12-15)

### ፪. የሰይጣን የውጊያ መንገዶች

#### ሀ. ሐሳብ

ሰይጣን በዔደን ገነት ሔዋንን ሲፈትናት የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን ሐሳብ ወደ አእምሮዋ በማምጣት እንደ ሆነ እናነባለን (ዘፍ. 3፥4):: «እባብም ለሴቲቱ አላት፤ ሞትን አትሞቱም፤ ከእርሷ በበላችሁ ቀን ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ::» በተጨማሪም የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀናል:: «ነገር ግን እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት ሐሳባችሁ ተበላሽቶ (በጠላት ሐሳብ ማለት ነው) ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ::» (2ቆሮ. 11፥3)

ሰይጣን መንፈስ (ክፉ መንፈስ) ስለ ሆነ፣ ሰውም በፍጥረቱ መንፈሳዊ ክፍል ስላለው (1ተሰ. 5፥23)፣ ሰይጣን ክፉን ሐሳብ ለሰው ያቀርባል:: ነገር ግን ክፉን ሐሳብ ማቅረብ እንጂ አማኙን ለማስገደድ ሥልጣን የለውም:: ያልነቃና ያልተዘጋጀ ክርስቲያን የጠላት ሐሳብ መሆኑን ሳያውቅ ከራሱ እንደ መነጨ አድርጎ ይቀበለዋል:: «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ... በሰማያዊ ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ::» (ኤፌ. 6፥12)

**አማኝ የሰይጣንን ክፉ ሐሳብ እንዴት ሊቋቋም ይችላል?**

1. ዘወትር በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ ሆኖ የሚመላለስ ክርስቲያን ከሰይጣን የሆነውን ሐሳብ ለይቶ ያውቃል:: «በሰይጣን እንዳንታለል፣ የእርሱን ሐሳብ አንስተውምና::» (2ቆሮ. 2፥11)

2. ዘወትር በእግዚአብሔር ቃል የሚሞላ ክርስቲያን ሐሳቡ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይሆናል። «መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካምን ነገር ያወጣል።» (ማቴ. 12÷33-35)

3. ዘወትር በመንፈስ የሚመላለስ ወይም ለመንፈስ ቅዱስ የሚታዘዝ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ነገር ያስባልና ለክፉ የጠላት ሐሳብ ስፍራ የለውም። «እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ የመንፈስን (የመንፈስ ቅዱስን) ነገር ያስባሉ።» (ሮሜ 8÷5)

ስለዚህ አማኝ በጸሎት፣ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሰይጣንን ክፉ ሐሳብ ሁሉ ሊቋቋምና ሊያሸንፍ፣ ኀይልም ሥልጣንም ተሰጥቶታል።

## ለ. ሥጋ

የሥጋ ፈተና ኀጢአትን፤ ኀጢአት ደግሞ ከእግዚአብሔር መለየትን እንደሚያመጣ ስለሚያውቅ፤ ሰይጣን አማኝን በሥጋው ይፈትነዋል። (ሥጋዊ) ምኞት ፀንሳ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች። (ያዕ. 1÷15) «... እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበር...» (ኤፌ. 2÷3)፤ «የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው፤ እርሱም ዝሙት ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቍጣ፣ አድመኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት ይህንም የሚመስል ነው።» (ገላ. 5÷19-21)፤ «በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ... በመንፈስ ብንኖር፣ በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ» (ገላ. 5÷16፡25)

## ሐ. ክስ

በዕብራይስጥ ቋንቋ ሰይጣን ማለት ከሳሽ ማለት ነው።
ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት በቀረበ ቍጥር ለክስ ወይም ለሙግት እንደ ሆነ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እናያለን።

- ጻድቁን ኢዮብን ከሰሰ (ኢዮ. 1÷6)፤
- ታላቁን ካህን ኢያሱን ከሰሰ ዘካ. (3÷1)።

በዮሐንስ ራእይ ሰይጣን ከሰማይ በተጣለበት ጊዜ፣ «ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሏል» የሚል ቃል እናነባለን። (ራእ. 12÷10)

ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያልተረዳ አማኝ በእግዚአብሔር ይቅር ከተባለ በኋላ እንኳ ባለፈው ኀጢአቱ ራሱን እየከሰሰና እየወነጀለ፣ በደካማነትና በውድቀት ስሜት እየተጨቈነ እንዲኖር ኅሊናውን በክስ ያወናብዳል።





የክርስትና እምነት ዋና መሠረት የሆነውና ከሌሎች ሃይማኖቶች ተወዳዳሪ የሌለው የሚያደርገው የእግዚአብሔር ምሕረት ነው።

«ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና» (ሮሜ 5÷8)
«የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኀጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ ... በኀጢአታችን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዐመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።» (1ዮሐ. 1÷7-9)

«ልጆች ሆይ! ኀጢአትን እንዳትሠሩ እጽፍላችኋለሁ፤ ነገር ግን ኀጢአትን ብንሠራ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» (1ዮሐ. 2÷1)

«ከኀጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።» (ዕብ. 4÷15) «ስለዚህ የሕዝብን ኀጢአት ለማስተስረይ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፣... እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።» (ዕብ. 2÷17-18)

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ (ፍርድ) የለባቸውም» (ሮሜ 8÷1)

## መ. የስሕተት ትምህርቶች

የሰይጣን ትልቁ መሣሪያ የስሕተት ትምህርት ነው። የስሕተት ትምህርት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ዐይነት ጠባዮች አሉት፤

1. የወንጌልን መልእክት ለማዳከምና ለመከለስ ይሞክራል፤
2. ቤተ ክርስቲያንን ይከፋፍላል፤
3. ወደ ተሳሳተ የሰይጣን አምልኮ ይመራል፤
4. የክርስቶስን አምላክነት ይቃወማል፤
5. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ይክዳል፤
6. የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ይቃወማል፤
7. ሥላሴን (ሦስትነትን) ይክዳል፤
8. በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በተገኘው «ደኅንነት» ላይ ሌላ ሥርዐትና የሕግ ሥራ ይጨምርበታል።
9. ትኵረቱ በክርስቶስ ላይ ሳይሆን በመሪው ወይም በነቢይ ነኝ ባዩ ላይ ነው። ከሚታወቁት የሐሰት እምነቶች መካከል እስላም፣

የዐዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ፣ የያህዌ ምስክሮች፣ ሞርሞንና፣ «ኢየሱስ ብቻ» ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

## ፫. <u>በአንጻሩ ወንጌል እንዲህ ይላል</u>:-

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታም አምላክም ነው፤
2. ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤
3. ደኅንነት (የዘላለም ሕይወት) በጌታ በኢየሱስ በማመን ብቻ ይገኛል፤ እርሱም ስለ ኀጢአታችን ሞቶ በአሸናፊነት ከሞት ተነሣ፤ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ በግርማው ተቀመጠ፤
4. ጌታ ኢየሱስ በዐይን በሚታይ ሁኔታ በደመና በመላእክት ታጅቦ ቤተ ክርስቲያንን (ልጆቹን) ለመውሰድ ዳግመኛ ይመጣል፤
5. መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ ነው፤
6. መንፈስ ቅዱስ ዛሬም በአማኞች ሕይወት ይሠራል::

## ፬ <u>ለአማኝ የተሰጠው መፍትሔ ምንድን ነው?</u>

አማኝ ሁሉን እንዲመረምርና እንዲፈትን ሥልጣንና ትእዛዝ ተሰጥቶታል:: «ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና::» (1ዮሐ. 4÷1) በተጨማሪም የእግዚአብሔር ቃል፣ «ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፤ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል:: <u>ሰይጣንን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል</u>» (ያዕ. 4÷7-8) በማለት ሰይጣን ተሳዳጅ እንጂ አሳዳጅ መሆን እንደሌለበት ያስተምረናል:: በሮሜ 16÷20 ላይም፣ «የሰላምም አምላክ <u>ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቀጠዋል» ይላል::</u>

በዮሐ. 16÷11 ደግሞ የዚህ ዓለም ገዥ (ሰይጣን) እንደ ተፈረደበት ይናገራል:: ይህ ሁሉ የሚያሳየን አማኝ የተሰጠውን ሥልጣን <u>ባለማወቅ</u> ለሰይጣን በር ካልከፈተ በስተቀር፣ ሰይጣን በአማኝ ላይ ሥልጣን እንደሌለው ነው (ሉቃ. 10÷19)::

አማኝ መታጠቅ ያለበትን መንፈሳዊ የጦር መሣሪያዎች (በኤፌ. 6÷10-18) እናነባለን፤

«በቀረውስ በጌታና በኀይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ:: <u>የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ</u> እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ:: መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፣ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር፣ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ:: ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ:: እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላፃዎች





ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፣ የመዳንንም ራስ ቍር፣ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም <u>የእግዚአብሔር ቃል ነው:: በጸሎትና</u> በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ::»

## ፭. <u>የአማኝ ሥልጣን</u>

አማኝ ስንል ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወቱ አዳኝ እንደ ሆነ አምኖ በንስሓና በእምነት ኢየሱስ ክርስቶስን በመቀበል የዘላለምን ሕይወት ያገኘ ማለታችን እንጂ በአፉ ብቻ አምናለሁ የሚለውን ሰው ማለታችን አይደለም::

አንድ አማኝ ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ ወደ ሕይወቱ በሚጋብዝበት ቅጽበት የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን እንደሚቀበል የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል:: «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው::» (ዮሐ. 1÷12) በዚህ በእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ውስጥ ለአማኝ የተሰጠው ሥልጣን ምን እንደ ሆነ እንመልከት:: አንድ የንጉሥ ልጅ በአባቱ መንግሥት ውስጥ እስካለ ድረስ ምንም ዐይነት ችግርና ጠላት ቢያጋጥመው፣ የንጉሡ ልጅ በመሆኑ ብቻ የአባቱ ሥልጣን እንዳለለት ያውቃል:: በራሱ ኀይልና ሥልጣን ሳይሆን ከአባቱ ባገኘው ኀይልና ሥልጣን ይመካል:: አንድ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር ልጅ ስለ ሆነ ብቻ የነገሥታት ንጉሥ ከሆነው ከሰማያዊ አባቱ የተሰጠው ሥልጣን አለው:: ምንም ዐይነት ችግርና ጠላት ቢመጣበት ጳውሎስ እንዳለው፣ «ኀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፤» (ፊል. 4÷13) ማለት ይችላል:: በተጨማሪም በኤፌ. 6÷10፣ «በቀረውስ <u>በጌታና በኀይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ</u>::» የሚለው ለዚህ ነው:: የምንበረታው ወይም የምንመካው በጌታ ኀይልና ችሎት እንጂ በራሳችን አይደለም:: ይህ የተሰጠን የልጅነት ሥልጣን ምንድን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃ. 10÷19 ላይ፣ «እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጐዳችሁም ምንም የለም::» በማለት ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውን ሙሉ ሥልጣን ያሳየናል:: ሔዋንን በዔደን ገነት ባሳታት በእባብ (በዲያብሎስ) ላይ አማኝ ሥልጣን ተሰጥቶታል ማለት ነው::

## <u>የአማኝ ሥልጣን የሚገለጸው</u>:-

### 1. <u>በኢየሱስ ክርስቶስ ስም</u>

የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆንን የአባታችንን ስም የመጥራትና የመጠቀም የልጅነት መብት አለን:: በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን ሳያገኙ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በአጋንንት ላይ ለመጥራት የሞከሩ አንዳንድ ሰዎች ምን ዐይነት ሽንፈት እንደ ደረሰባቸው በሐዋ. 19÷13-16 ማንበብ እንችላለን፤ «ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናምላችኋለን እያሉ ክፉዎች መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን ስም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ:: ... ክፉው መንፈስ ግን መልሶ፣ ኢየሱስንስ ዐውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ እናንተሳ

እነማን ናችሁ? አላቸው፡፡ ክፉው መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው ቈስለውም ከዚያ ቤት ዕራቍታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው፤ አሸነፋቸውም፡፡» ይላል ቃሉ፡፡ ይህ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ሳይኖራቸው ስሙን ለመጥራት ስለ ሞከሩ ነው፡፡ የልጅነት ሥልጣን ያላቸውን አማኞች ሁሉ ግን ጠላት ማን መሆናቸውንና የጌታን ስም ለመጥራት መብትና ሥልጣን እንዳላቸው ያውቃል፡፡

## በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውስጥ ምን ዐይነት ሥልጣን አለ?

ፊል 2፥9-11፣ «… እግዚአብሔር (ክርስቶስ ኢየሱስን) ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» ይላል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክለትና የሚብረከረክለት ስም ነው፡፡ የእርሱ ስም ሲጠራ በፊቱ የማይንበረከክ ኀይል የለም፡፡

«ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይላትም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው፣ በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፡፡ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን (ለአማኞች) ሰጠው፡፡ እርስዋም (ቤተ ክርስቲያን) አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላት ናት፡፡» (ኤፌ. 1፥19-23)

ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ፣ ሁሉ የሚንበረከክለትና ከእግሩ በታች የሚገዛለት ስም ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ወይንም አማኞች የክርስቶስ አካል ስለ ሆኑ፣ ከክርስቶስ እግር ሥር የሆነ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያንም እግር ሥር ነው፡፡ የአካሉ ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ አካሉ ግን ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ «ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት» ሲል ሰይጣን ከቤተ ክርስቲያንም እግር ሥር ነው ማለቱ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናትና፡፡

በሮሜ 10፥13 ላይ፣ «የጌታን ስም  የሚጠራ ሁሉ ይድናል፡፡» የሚል ቃል እናነባለን፡፡ ይህ ቃል ስለ ነፍስ መዳን ብቻ ሳይሆን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከማንኛውም ክፉ ነገር የምንድንበት እንደ ሆነ ነው የሚያሳየን፡፡ በብሉይ ኪዳንም እንኳ የእግዚአብሔር ሰዎች በእግዚአብሔር ስም ምን ዐይነት ድል እንዳገኙ ማየት እንችላለን፡፡ በ1ሳሙ. 17፥45 ዳዊት በእግዚአብሔር ስም ጎልያድን እንዴት እንዳሸነፈ እናነባለን፡፡ «ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን አለው፤ አንተ ጦር፣ ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ፡፡»

«አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ፤ በእግዚአብሔር ስም አሸነፍኋቸው፤ መክበቡንስ ከበቡኝ፤ በእግዚአብሔር ስም አሸነፍኋቸው፣ ንብ ማርን





እንዲከብብ ከበቡኝ፤ እሳትም በእሾህ ውስጥ እንዲነድድ ነደዱ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው፡፡» (መዝ. 117(118)፥10-12)፡፡

«እነዚያ በሠረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ፤ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን፡፡ እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ፤ እኛ ግን ተነሣን፤ ጸንተንም ቆምን፡፡» (መዝ. 19(20)፥7-8)

«የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው፣ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል፡፡» (ምሳሌ 18፥10)

በስሙ ውስጥ ያለውን ሥልጣንና ክብር ዐውቆ የሚጠራውን እግዚአብሔር እንደሚጋርድ ቃሉ ይነግረናል፡፡ «በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ፤ ስሜንም ዐውቆአልና እጋርደዋልሁ፡፡» (መዝ. 90(91)፥14)

## 2. በእግዚአብሔር ቃል

«የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሐር ቃል ነው፡፡» (ኤፌ. 6፥17)

«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፤ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፤ ነፍስንና መንፈስንም፣ ጅማትንም ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፤ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፡፡» (ዕብ. 4፥12)

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰይጣን በተፈተነበት ጊዜ ሦስቱንም ፈተናዎች ያሸነፈው፣ «ተጽፎአል»፤ «ተጽፎአል»፤ «ተጽፎአል» በማለት ነበረ፡፡ ሦስቱንም ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል ነበረ የጠቀሰለት፡፡ ቃሉ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ስለ ሆነ ጠላትን የመቍረጥና የመውጋት ኀይል አለው፡፡ በዮሐንስ ራእይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ሲገልጽ፣ «ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ወጣ» (ራእ. 1፥16) የሚል ቃል እናነባለን፡፡ ከኢየሱስ አፍ የሚወጣው ቃል ተራ ቃል ስላልሆነ እንደ ስለታም ሰይፍ ጠላቶቹን የሚቈራርጥ ነው፡፡ በዚህ ቃል ውስጥ ያለው ሥልጣን ለእኛም ተሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ ነው «የመንፈስን ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው፤» የሚለን (ኤፌ. 6፥17)፡፡

በተጨማሪም፤ ቃሉ ጨለማን የመግፈፍ ኀይል ያለው እንደ ሆነ እናያለን፡፡ «ሕግህ (ቃልህ) ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴም ብርሃን ነው፡፡» (መዝ. 118(119)፥105)

ሕይወቱን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የመሠረተ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል የሕይወቱ መመሪያ ያደረገ ሰው ምንም ዐይነት የጠ ላት ጐርፍና ዐውሎ ነፋስ ቢመጣበት አይበገርም፡፡ «ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል፡፡ ዝናብም ወረደ፤ ጐርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት ገፋው፤ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም፡፡» (ማቴ. 7፥24-25)

### 3. <u>በኢየሱስ ክርስቶስ ደም</u>

በደሙ ውስጥ ያለው ኀይልና ሥልጣን ኀጢአትን ሁሉ የሚያነጻ ነው:: «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል::» (1ዮሐ. 1÷7)

ኀጢአት በሕይወታችን ካለ ለጠላት ስለምንጋለጥና በጠላት ስለምንጠቃ፣ ኀጢአትን ቶሎ ከሕይወታችን የምናስወግድበት ኀይል ንስሓና የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው:: በብሉይ ኪዳን የነበረውን የእንስሳት ደምና በዐዲስ ኪዳን የፈሰሰልንን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም በማወዳደር የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፤ «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር ዐመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ ከሆኑ፣ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ኅሊናችሁን ያነጻ ይሆን?» (ዕብ. 9÷13-14) ኀጢአት ኅሊናችንን አርክሶ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት በሚወሰድበት ጊዜ፣ ሰይጣንም ያለ ማቋረጥ በሚከሰን ጊዜ፣ ኅሊናችንን ፈጽሞ ማንጻት የሚችለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ደም ብቻ ነው::

## <u>የተሰጠንን ሥልጣን እንዳንጠቀም የሚያደርጉን ነገሮች፦</u>

### ሀ. <u>ኀጢአት</u>

ኀጢአት ከእግዚአብሔር ስለሚለየን (ኢሳ. 59÷1-2) ከእርሱ ያገኘነውን ኀይልና ሥልጣን መጠቀም አንችልም:: ያለን አማራጭ በንስሓ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መንጻትን መቀበል ነው::

ሳምሶን ከእግዚአብሔር ተሰጥቶት የነበረውን ታላቅ ሥልጣን በኀጢአት ምክንያት እንዳጣው የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል::

«እርስዋም፣ ሳምሶን ሆይ! ፍልስጥኤማውያን መጡብህ አለችው:: ከእንቅልፉም ነቅቶ፣ እወጣለሁ፤ እንደ ወትሮውም አደርጋለሁ አለ:: ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ተለየው አላወቀም::» (መሳ. 16÷20) እግዚአብሔር ከእኛ እንዲለይ የሚያደርግ ኀጢአት ነው::

### ለ. <u>አለማወቅ</u>

ምናልባት፣ አለማወቅ የክርስቲያኖች ዋነኛ ችግር ሳይሆን አይቀርም:: የእግዚአብሔር ቃል፣ «<u>ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል</u>» (ሆሴዕ. 4÷6) ይለናል:: በክርስቶስ የተሰጠንን ሥልጣን ካላወቅን እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ ባይተዋር መኖር እንችላለን:: በጠላት ላይ ሠልጥነን ሳይሆን፣ ጠላት በእኛ ላይ ሠልጥኖብን እንኖራለን:: በጠላት ላይ ተጫምተን ሳይሆን፣ ጠላት እየተረማመደብን እንኖራለን:: አለማወቅ የንጉሥን ልጅ እንደ ለማኝና እንደ ባሪያ እንዲኖር ያደርገዋል::

**በተሰጠን ሥልጣን እንድንኖር እግዚአብሔር ይርዳን::**





## <u>ትምህርት ስድስት</u>

## <u>መንፈሳዊ ውጊያና የአማኝ ሥልጣን</u>

የመታወቂያ ቍጥር፤ ________________________

ስም፤ ________________________

አድራሻ፤ ________________________

________________________

________________________

1. ክርስቲያን ውጊያ እንዳለበት የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል:: መንፈሳዊ ውጊያ ማለት ምን ማለት ነው?

2. የክርስቲያን ውጊያ ከጠላት ከዲያብሎስ ጋር ነው:: ዲያብሎስ አማኞችን የሚዋጋው በምን በምን መንገድ ነው? ከዘረዘርሃቸው ውስጥ አንተን የበለጠ የሚመለከትህን አንዱን አብራራ::

3. ሰይጣን አማኝን የሚዋጋበት አንዱ መንገድ ክፉ ሐሳብ በአእምሮው በማምጣት ስለ ሆነ፣ አማኝ ሰይጣን የሚያመጣበትን ክፉ ሐሳብ እንዴት መቋቋም ይችላል?

4. እግዚአብሔር ለአማኞች የሰጠው ሥልጣን በምን በምን መንገድ ይገለጣል? እያንዳንዱ ምን እንደ ሆነ በዐጭሩ አስረዳ::

5. አማኝ በሰይጣን ላይ የተሰጠውን ሥልጣን እንዴት መጠቀም አለበት?

6. አማኝ የተሰጠውን ሥልጣን መጠቀም እንዳይችል የሚያደርጉት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

7. መንፈሳዊ ውጊያ ግልጽ በሆነ መንገድ አጋጥሞህ ከሆነ፣ ምን እንደ ሆነና እንዴት ድልን እንዳገኘህ በዐጭሩ አስረዳ::

8. እግዚአብሔር የሰጠህን ሥልጣን በዕለታዊ ኑሮህ እንዴት እየተጠቀምህበት ነው?